ዲሞክራሲ የለም፣ አይኖርምም፤ ሰላም ደብዛዋ እንደጠፋች ትቀያለች። ረሀብ፣ ድህነት፣ በሽታ፣ ጦርነት ይቀጥላሉ:: ጨለማው አለ፣ ይቀጥላል:: ከደይኑ ባሻገር የምትታየው ኮከብ ትላንትም ሆነ ዛሬ በተሰውትና በሚሰዉት የህዝብ ታጋዮች ደም የምትበራ ናት:: ብርሃን ተጠናክሮ ጨለማውን ለማጥፋት ትችል ዘንዱ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ተባብሮ ክንዱን አጠናክሮ ዱር ቤቴ ብሎ ብረት አንስቶ በቆራጥ ጀግኖች መስዋዕትነት አርአያ እየተገፋፋ አምርሮ መታገል ያሻል:: የካቲት አልፎ የካቲት ሲተካ የመከራና የስቃይ ዝክር ከማዱረስ መገላገያው መንገዱ ይህ ብቻ ነው::

የየካቲት 66 አብዮት በህዝብ ትግል ሙሉ ድልን ይቀዳጃል!!

በህብረት ቆርጦ የሚታገል ህዝብ ባለድል ይሆናል!

እናሸንፋለን!!